በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

**ጠ/ሚር ጽቤት ርዕሰ አንቀጽ**
**የካቲት 2013**

# ከሥነ ውበት ባሻገር

በኮይሻ መንደር ነዋሪ የሆኑት በቀለች አሕመድ ባል የሞተባቸው እና የሦስት ልጆች እናት ናቸው። “አዲስ እና አስደሳች ዕድሎች የትውልድ መንደሬን ሊያጥለቀልቋት ነው” ይላሉ። የተሻለ የኢኮኖሚ ዕድሎች ለመፈለግ ሦስት ልጆቻቸውን እና ቤተሰባቸውን ትተው ወደ አቅራቢያ ከተማ ከገቡ ከራርመዋል። ኮይሻ ከአረንጓዴ ኮረብታዎቿ እና ከጠመዝማዛ ሜዳዎቿ እስከ ለምለም ደኖቿ በኢትዮጵያ ውስጥ ገና ያልተነኩ የኢንቨስትመንት ዕምቅ ሀብቶችን አንዱን ትወክላለች። የቱሪዝም ገቢን ለማመንጨት ሊዳበሩ ከሚችሉ ግዙፍ የተፈጥሮ ገጽታዎች በተጨማሪ አካባቢው ለግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች መሠረት የሚሆን ነው ። እንደ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ፓፓያ፣ አናናስ እና ፖም ያሉ የተለያዩ የፍራፍሬ ተክሎችን እሴት በመጨመር ምርትን የማሳደግ ዐቅሙ እጅግ ከፍተኛ ነው።

ምድረ ቀደምት እና የዓባይ ምንጭ እንደመሆኗ መጠን ኢትዮጵያ ልዩ እና የተረጋጋ የቱሪዝም እና የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንድትሆን የሚያስችሉ አስደናቂ ተፈጥሯዊ ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ዕንቁዎች በብዛት ይዛለች። እነዚህን የተለያዩ እና ሰፊ ሀብቶች ብትይዝም ሀገሪቱ እንደ ኮይሻ ባሉ የቱሪዝም መዳረሻዎች ውስጥ የሚኖሩ የአካባቢ ማኅበረሰቦችን ለመደገፍ ሙሉ በሙሉ አልተንቀሳቀሰችም።

የ‘ገበታ ለሀገር’ መርሐ ግብር በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መጀመሩ እንደ በቀለች ያሉ ከቤተሰቦቻቸው የተለዩ ብዙዎች አንድ ቀን ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ አዲስ ተስፋ የሚሰጥ እና የናፈቃቸውን ዕድል እንዲያገኙ የሚያስችል ነው።

በጠቅላይ ሚኒስትሩ የግል አነሣሽነት የተጀመረው ‘ገበታ ለሀገር’ ተለይተው በሚታወቁ ሦስት ስፍራዎች ላይ እንደ መንገድ እና ኤሌክትሪክ ያሉ ወሳኝ መሠረተ ልማቶችን ይዘረጋል። ለዚህ ደግሞ ገንዘብ ለማሰባሰብ የሀገር ውስጥ የግል ዘርፉን አስተባብሯል። የጠቅላይ ሚኒስትሩን መርሐ ግብር በአቀራረብ ልዩ የሚያደርገው ለእነዚህ ጣቢያዎች ልማት የመንግሥት ፋይናንስን አለመጠቀሙ ነው።

ሌላዋ የ"ገበታ ለሀገር" መዳረሻ ጎርጎራ ሰፊ ታሪክ እና ተፈጥሮአዊ ስጦታ የተጎናጸፈች ታሪካዊት የወደብ ከተማ ናት። ከተማዋ ከጎንደር 65 ኪሎ ሜትር የአስፋልት መንገድ ርቀት ላይ የምትገኝ ሲሆን በምሥረታ በሀገሪቱ ካሉ 10ቱ የቱሪስት መዳረሻዎች አንዷ ከሆነችው ከጎንደር ከተማ ትቀድማለች። ከተማዋ በአስደናቂ መልክአ ምድራዊ አቀማመጧ፣ በለም መሬቷ እና በልዩ ልዩ ማኅበረሰቦቿ ምክንያት በአንድ ወቅት እጅግ የደራ የገበያ ቦታ ነበረች።

ብዙዎቹ የጎርጎራ ነዋሪዎች በአሁኑ ጊዜ ከመንግሥት በሚያገኙት አነስተኛ ገንዘብ የሚተዳደሩ ጡረተኞች ናቸው። አሳዬኸኝ አስቻለው በከተማዋ የሚኖሩ አዛውንት ሲሆኑ የ‘ገበታ ለሀገር’ መርሐ ግብር፣ ሥራ ፍለጋ ከተማዋን ለቅቆ የወጣውን እና ቅር የተሰኘውን ወጣት እንደገና ያነቃቃል ይላሉ። 'እኔ ዕድሜዬ የገፋና ቀሪው ዘመኔም አነስተኛ ነው፣ ግን ፕሮጀክቱ የከተማዋ ወጣቶች ከተማዋን ወደ ቀደመው ክብሯ ለመመለስ እንዲችሉ ይረዳቸዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ' ይላሉ።

ሌላው በመንግሥት የተለየው ቁልፍ ፕሮጀክት የወንጪ እና ደንዲ ልማት ነው። የውብ ሸለቆ ሐይቆች ፣ ፍል ውኃ ምንጮች እና ፏፏቴዎች መገኛ የሆነው ይህ የእሳተ ገሞራ ስፍራ ለዓመታት በጣም አነስተኛ ጎብኚዎችን አስተናዷል።

በወንጪ ከተማ ነዋሪ የሆነው አናጺው ፈይሳ ደገፋ " ይህን ቦታ ለማልማት ከፍተኛ ጥረት ቢደረግ ኖሮ በዓለም ላይ ካሉት እጅግ ውብ ስፍራዎች አንዱ ነው " ይላል። ስለ ተወዳጁ ከተማው ሲናገርም ፣ መንግሥት ወንጪን ከልማት ፕሮጀክቶች መካከል አንዷ እንድትሆን በመለየቱ መደሰቱን እየገለጸ የሚጠበቀውን የቱሪስት ፍሰትን እና ሌሎች የጎብኝዎችን ፍላጎት ለማሟላት ጠንክሮ በመሥራት የተዳከመ ቢዝነሱን መገንባት እንደሚችል ተስፋውን ይገልጻል።

በ2011/2012 ውስጥ ብቻ ከ 850,000 ሺህ በላይ ዓለም አቀፍ ጎብኚዎች ኢትዮጵያን ጎብኝተው ኢንዱስትሪው ከ 160,000 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥሯል። ሆኖም የ COVID19 ወረርሽኝ በዚህ ዓመት ለዘርፉ ዕንቅፋት ሆኗል። በወረርሽኙ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ውስጥ ከቱሪዝም የተገኘው ገቢ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በጣም ቀንሷል።

ዘርፉ በድኅረ COVID19 ወረርሽኝ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያገግም ይጠበቃል። በሚቀጥሉት ዐሥር ዓመታት ኢትዮጵያ በዘርፉ የተፈጠሩ ሥራዎችን ከሦስት እጥፍ በላይ ለማሳደግ ፤ የሀገር ውስጥ ጎብኝዎችን ቁጥር በእጥፍ ለመጨመር እና በ 2011/2012 ከተመዘገቡት ዐሥር እጥፍ በላይ የዓለም አቀፍ ጎብኚዎችን ቁጥር ለመጨመር ትጠብቃለች፡፡

ዘርፉ ወሳኝ መሠረተ ልማት ፣ ጥበቃ ፣ ግብይት እና የአመራር ተግዳሮቶች ያሉበት በመሆኑ ግን ይህ ወሳኝ ጥረት ከችግሮች የጸዳ አይሆንም። እነዚህንና ሌሎች ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ሀገሪቱ በ10 ዓመቱ ዕቅዷ የቱሪዝም መዳረሻ መሠረተ ልማቶችን ማልማት እና የግሉ ዘርፍን ሚና ማሳደግ ወሳኝ የትኩረት አቅጣጫዎቿ ናቸው። በ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የተጀመሩ እንደ “ገበታ ለሀገር” ያሉ ኮይሻ ፣ ጎርጎራ እና ወንጪ ያሉ ቦታዎችን ለማልማት የታቀዱ ጅምር ዘርፎች ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ቁልፍ ከሆኑ ምንጮች አንዱ እንዲሆኑ ማድረግ ተጨማሪ ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው። በተመሳሳይም ሦስቱም ቦታዎች ለተቀናጀ የማምረቻ እና በአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንቨስትመንት መዳረሻ የመሆን ሰፊ ዕድል ይፈጥራሉ።

እነዚህ ፕሮጀክቶች ዘላቂ ልማት ለማምጣት፣ በዘርፉ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ኢንቨስትመንትን በማነቃቃት፣ የተገለሉ ማኅበረሰቦችን በማብቃት፣ ባህላዊ እና አካባቢያዊ ቅርሶችን በመጠበቅ፣ እና በተዛማጅ ዘርፎች ውስጥ እና በአጠቃላይ የግል እና የመንግሥት አጋርነቶችን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው።

//